ክብረ ቅዱሳን

# የነቢዩን ራስ ለዘፋኝ ወሮታ

ከዓልአዛር ግርማ

ልዑል እግዚአብሔር በልብ የመከረውን ድኅነተ ዓለም በየ ጊዜው በተነሱ ነቢያት አማካኝነት ምሳሌ እያስመሰለ ሱባዔ እያስቆጠረ ትንቢት እያናገረ ለሰው ዘር ያስረዳ ነበር ። ነቢያትም መንፈስ እግዚአብሔር እንደመራቸው በብዙ ኅብረ አምሳል በብዙ ኅብረ ትንቢት የምሥጢረ ሥጋዌን ነገር ገልጸው ትንቢቱ ከሚፈጸምበት ምሳሌው ከሚተረጐምበት ዕለት ሳይደርሱና ትንቢት የተነገረበትን ምሳሌ የተመሰለለትን ጌታ ሳያዩ አልፈዋል ። እነዚህ ነቢያት የተነበዩትን ጌታ በዓይነ ሥጋቸው ባያዩትም በትንቢት በምሳሌ እንዳዩት ቆጥረው ተደስተዋል ። ነቢያቱ ሁሉ በተለያየ መንገድ ይግለጹት እንጅ ዓላማቸው የፈጣሪን ሰው መሆን የሚያበስሩ ናቸው ።

እግዚአብሔር የወሰነው ዘመን ሲደርስ ያ! ነቢያት ትንቢት የተናገሩለት አዳኝ ከመወለዱ በፊት በነቢያት ፥ በመልአክና በእግዚአብሔር የተመሰከረለት አንድ ህፃን ተወለደ ። ይህ ህፃን ዮሐንስ ይባላል ። በአዲስ ኪዳን በዚህ ስም የሚጠሩ ሌሎችም ሰዎች ስለአሉ ከእነሱ ለመለየት ዮሐንስ መጥምቁ ይባላል ከቅዱሳት መጻሕፍት ያገኘነውን የዮሐንስን ታሪክ በአጭሩ እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል ።

ከአብያ ወገን ተሹመው ከሚያገለግሉት ወገን የሚሆን ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበር ሚስቱም ከአሮን ወገን የምትሆን ኤልሳቤጥ ትባል ነበር ። ሁለቱም እግዚአብሔር በሚወደው ሕግ ጸንተው የሚኖሩ ደጋግ ሰዎች ነበሩ ። ሚስቱ ኤልሳቤጥም መካን ነበረች ። ሁለቱም ልጅ ይሰጣቸው ዘንድ ሁሉን ማድረግ ወደሚችል እግዚአብሔር ዘወትር ይጸልዩ ነበር ። ሁለቱም በእድሜአቸው አርጅተው ይወልዳሉ ተብሎ ከማይገመትበት ዕድሜ ደርሰው ነበር አንድ ጊዜ ዘካርያስ ቤተ መቅደስ የሚያጥንበት ተራው (ሰሞኑ) በደረሰ ጊዜ እንደተለመደው ከቤተ መቅደስ ገብቶ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ በማጠን ላይ ሳለ ሕዝቡ ደግሞ በውጭ ሆነው ይጸልዩ ነበር ።

በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በመሰዊያው ቀኝ በኩል ታየው ዘካርያስ መልአኩን ባየው ጊዜ ደነገጠ መልአኩም ዘካርያስ ሆይ አትፍራ አለው ለመልአክ ፍርሃትን አርቆ መናገር ልማድነውና ። ልጅ ስጠኝ በማለት የለመንከው ልመና ተሰምቶልሃል ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙን ዮሐንስ ትለዋለህ ብዙዎችን በትንቢቱ በትምህርቱ ያስደስታል የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል ። እሱም መክሮ አስተምሮ ከእስራኤል ወገን ብዙ ሰዎችን ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ይመልሳቸዋል በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በኤልያስ ግብርጸንቶ መንፈቅ ተቀድሞ ያስተምራል አለው ።

ዘካርያስም ይህን በሰማ ጊዜ ነገሩን ተጠራጥሮ ምልክት ሽቶ ሁለታችንም አርጅተናል ልጅ እንምንወልድ በምን አውቃለሁ አለው እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤልነኝ በጊዜው የሚፈጸመው ቃሌን ስላላመንህ ይህ ሁሉ እስኪደረግ ድረስ ድዳ ትሆናለህ በማለት ከገሠጸው በኋላ ምልክት ሽቶ ነበርና ድዳ አደረገው ። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ድዳ ሆነ ።

ዘካርያስም የሚያጥንበት ተራውን ፈጽሞ ወደቤቱ ተመለሰ ከዚያም ሚስቱ ኤልሣቤጥ ጸነሰች በዚህ ወራት ስድቤንና መናቄን ከሰው ያርቅልኝ ዘንድ በረድኤት ጐበኘኝ በማለት ጽንሱ በደንብ እስከሚታወቅ ፭ ወር ራሷን ሸሸገች በስድስተኛው ወርዋ እመቤታችን ቅ/ድንግል ማርያም መልአኩ ቅ/ገብርኤል እንደነገራት የኤልሳቤጥን መጸነስ ለማየት ዘካርያስ ታመመ ብለዋታልና ለመጠየቅ እንዲሁም የአምላክን ሰው መሆንና የእሷን ወላዲተ አምላክነት ከቅ/ገብርኤል በተጨማሪ በኤልሳቤጥና በዮሐንስ ለማስመስከር ወደ ደጋማው የይሁዳ ምድር ወደዘካርያስ ቤት ሄደች ።

እመቤታችንም ዘካርያስ ቤት ደርሳ ኤልሳቤጥን እንዴት ሰነበትሽ አለቻት ኤልሳቤጥም የእመቤታችንን የሰላምታ ድምፅ እንደሰማች መንፈስ ቅዱስ መላባት ጽንሱም በማኅጸኗ ውስጥ በደስታ ዘለለ ። ይህንንም ሐዋርያት ሲኖዶስ በተባለው መጽሐፍ ዮሐንስ በእናቱ ማኅፀን ሳለ ሰገደ ብለዋል ቅ/ያሬድም እንዲሁ ሰገደ ብሎአል ይህም ዮሐንስ ገና የ፮ ወር ጽንስ ሳለ መልአኩ እንደ ተናገረው መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በእመቤታችን ማኅፀን ለተጸነሰው አምላክ የባሕርይ (የአምልኮት) ስግደት ለአምላክ እናት ለእመቤታችን ደግሞ የጸጋ ስግደት እንደሰገደ እንረዳለን ።

ቅ/ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ገልጾላት ከቅዱስ ገብርኤል አያይዛ አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እያማለድሽ የምታሰጪ ነሽ የማኅፀንሽ ፍሬም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የሚያድል የባሕርይ አምላክ ነው ። የጌታዬ እናት እመቤቴ ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ ምንድን ነኝ የሰላምታሽን ድምጽ በሰማሁ ጊዜ ጽንሱ በማህፀኔ በደስታ ዘሏልና ከእግዚአብሔር አግኝተው የነገሩሽን ነገር እንዲደረግ የምታምኝ አንቺ ብጽዕት ነሽ ብላ ውዳሴዋን ቅዳሴዋን አድርሳለች ።

የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ጊዜ

ደረሰና ወንድ ልጅ ወለደች በስምንተኛው ቀን ሊገርዙት መጡ ስምም ያወጡለት ዘንድ አባቱን ጠየቁት ዘካርያስም ብራና ይዞ ስሙን በብራናው ላይ መልአኩ እንደነገረው ዮሐንስ ብሎ ጻፈ ወዲያው አንደበቱ ተፈትቶ መንፈስ ቅዱስ ሞልቶበት ትንቢት ተናገረ ። በጐረቤቶችም ዘንድ ፍርሐት ሰፈነ ይህ ህጻን ምን ይሆን? አሉ ይህም ማለት እንደ ሙሴ ጠላት የሚገድል ባሕር የሚከፍል ደመና የሚጋርድ መና የሚያወርድ እንደ እያሱ በረዶ የሚያዘንም ፀሐይ የሚያቆም እንደኤልያስ ሰማይ የሚለጉም ዝናብ የሚያቆም እሳት የሚያዘንም ይሆንን አሉ ዘካርያስም በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ አንተ ህጻን የልዑል እግዚአብሔር ነቢይ ትባላለህ መንገዱንም ልትጠርግ በጌታ ፊት መንፈቅ ተቀድመህ ታስተምራለህ በማለት ትንቢት ተናገረ (ሚል ፬.፭ ሉቃ. ፩፡፲፯ ሉቃ ፩፡፩-፹)

ከዚያም በጌታ ልደት ምክንያት ሄድሮስ ሕፃናትን በሚያስፈጅበት ሰዓት ዘካርያስ ህጻኑን ዮሐንስን ከቤተመቅደስ አግብቶ ሲጸል



የነብዩ አንገት ተቆርጦ ለሄሮድያዳ ሲበረከት



የሰማዕታት ክብራቸው ስለ ፈጣሪያቸው ምድራዊ መከራን መቀበል ነው

ይለት ሄድሮስ ግደሉ ብሎ ጭፍራ ላከበት ከቤቱ ቢሄዱ አጡት በኋላ መልአኩ ለእናቱ ለኤልሳቤጥ ይህ ዓላዊ ልጅሽን ሊገድለው ነውና ህፃኑን ይዘሽ ወደ ገዳም (በረሃ) ሂጂ ብሏት ዮሐንስን ይዛ በረሃ ሄዳለች ጭፍሮችዋ ከቤተመቅደስ መጥተው ዘካርያስን ብቻውን ሲያገኙት እሱን ከቤተ መቅደስ ውስጥ ገድለውታል ይህንንም ጌታችን በማቴ ፳፫፡፴፭ ላይ “ ... ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያዎች መካከል እስከገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችኋል” በማለት ተናግሯል ለሰማዕታተ ብሉይ ጀማሪያቸው አቤል ሲሆን ፍጻሜአቸው ደግሞ ዘካርያስ ነው ።

ዮሐንስም በገዳም ሳለ የበረሃ ማር እየበላ የግመል ጠጉር እየለበሰ በመንፈስና በጥበብ በጸጋም ያድግ ነበር ሠላሳ ዓመት ሊሞላው ጌታችን መንፈቅ ሲቀረው መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያት በልጅነት ፣ ልጅነት በሃይማኖት ልትሰጥ

ቀርባለችና እመኑ እያለ ያስተምር ጀመር ሕዝቡም ሁሉ ወደሱ እየመጡ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ያጠምቃቸው ነበር ። በነቢዩ በሚልክያስ እነሆ መልእክተኛዬን እልካለሁ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል ተብሎ እንደተነገረለት የአለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ከማስተማሩ ፮ ወር አስቀድሞ ማስተማር ጀመረ ። (ሚል፫፡፩ ማቴ ፲፩፡፲ በነቢዩ በኢሳይያስም እንደተገለጸው "የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ.. ዐዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይበል ጠማማውም የቀና መንገድ ይሁን ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሁን እያለ ሰውን ወደ ንስሐ ይጠራ ነበር ። (ኢሳ ፵፡፫-፭ ሉቃ ፫፡፮ )ትምህርቱን ተቀብለው ንስሐ የገቡትን የንስሐ ጥምቀት እያጠመቃቸው ለእውነተኛው መምህር ለኢየሱስ ክርስቶስ ለደገኛው ትምህርት ለቃለ ወንጌል ልጅነት ለምትሰጠው ለደገኛይቱ ጥምቀት ሕዝቡን ያዘጋጅ ነበር ።

ቅ/ዮሐንስ በሚያስተምርበት ጊዜ ራሱን ዝቅ ዝቅ እያደረገ ፈጣሪውን ክርስቶስን እያከበረ ያስተምር ነበር ለምሳሌ "እኔ ለንስሐ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ጫማውን እሸከም ዘንድ የ ማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ ይበረታል ።" (ማቴ. ፫፡፲፩) ሉቃ ፫፡፲፭-፲፯) እኔ በውሃ አጠምቃለሁ ዳሩ ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል እኔ የጫማውን ጠፈር ልፈታ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከበር ነው" (ዮሐ.፩፡፳፮ ፳፯) እያለ ይመሰክር ነበር ።

አንድ ቀን ዮሐንስ ጌታችን ወደእሱ ሲመጣ አይቶ "እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ "አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ነው ያልሁት ይህ ነው አለ ። "ዮሐ ፩፡፳፱-፴)

ጌታችን ፴ ዘመን ሲሞላው በእደ ዮሐንስ በማየ ዮርዳኖስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ሄደ ጌታችን ዮሐንስን አጥምቀኝ ባለው ጊዜ ዮሐንስ በትህትና "እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል እንጅ እንዴት አንተ በእኔ ትጠመቃለህ በማለት ቢከላከልም የፈጣሪውን ፈቃድ መፈጸም ስላለበት ፈጣሪውን ለማጥመቅ በቅቷል በዚህም የተነሳ መጥምቁ ዮሐንስ ወይም መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ተብሎ ይጠራል ይህ ዕድል (ጸጋ) ለማንም ያልተሰጠ በመሆኑ ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ የመድኃኒዓለም ትሕትና የዮሐንስ ክብር ዕፁብ ድንቅ በማለት ስታዘክር ትኖራለች (ማቴ ፫፡፲፫ -፲፯)

ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቁ ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት በማግባቱ ንጉሡን ሳይፈራ ሳያፍር የወንድምህን ሚስት ልታገባ አይገባህም በማለት ይወቅሰው ነበር ። በዚያም ምክንያት ሄሮድስ ተቆጥቶ ዮሐንስን አሳሰረው ዮሐንስም በወህኒ ታስሮ ሳለ ሁለቱን ደቀመዛሙርቱን ወደ ጌታችን "የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ ብሎ ላከ" ። ጌታም ለተላኩት ሰዎች "ሂዱና ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አወሩለት ዕውሮች ያያሉ ፣ አንካሶች ይሄዳሉ ፣ ለምጻሞች ይነጻሉ ፣ ሙታንም ይነሳሉ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል በኔም የማይሰናከል ሁሉ ብፁዕ ነው "ብላችሁ ንገሩት በማለት ነቢያት የተነበዩለት መድኃኒት የአምላክ ልጅ አምላክ መሆኑን መሰከረላቸው አረጋገጠላቸው ።

ዮሐንስ በእስር ላይ እንዳለ የሄሮድያዳ የልደቱ በዓል በሚከበርበት ዕለት ታላቅ ግብር አድርጎ ሳለ የሄሮድያዳ ልጅ ገብታ በበዓሉ ላይ ዘፈነችላቸው በዘፈኗም ሄሮድስንና በዚያ የተቀመጡትን መኳንንቶች በሙሉ አስደሰተቻቸው ሄሮድስም ለዘፈነችይቱ ብላቴና የምትወጅውን ሁሉ እስከ መንግሥቴ እኩሌታም ቢሆን እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት እሷም እናቴን አማክሬ ልናገር ብላ ሄዳ ሄሮድያዳን ንጉሡን ምን ልጠይቀው አለቻት እናቲቱም ቀድ